በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን

# ስታቲስቲክስና የማ.ስ.ባ የ1990 በጀት ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም አጭር መግለጫ

አዲስ አበባ
መስከረም 1991

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን

# ስታቲስቲክስና የማ.ስ.ባ የ1990 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም አጭር መግለጫ

አዲስ አበባ
መስከረም 1991

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

1. መግቢያ........................................................ 1

2. የስታትስቲክስ መረጃዎች ጥቅምና አስፈላጊነት.................................. 3

3. የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች........................................ 3

4. የስታቲስቲክስ ጥናቶች አፈፃጸም ቅደም ተከተል.................................5

5. የስታቲስቲክስ መረጃ ማሰራጫ ዘዴዎች........................................ 7

6. የማ.ስ.ባ የ1990 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ........................................ 8

7. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ................................. 20

8. የሰው ኃይል ሁኔታ ሥልጠና............................................... 21

9. የበጀት አጠቃቀም............................................................ 22

10. ማጠቃለያ................................................................. 23

# ስታቲስቲክስና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1990 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር መግለጫ

## 1. መግቢያ

የ1990 በጀት ዓመት ዕቅደ አፈጻጸምን አስመልክቶ በዝርዝር ከመታየቱ በፊት ለአጠቃላይ ግንዛቤ እንዲረዳ ስለ ስታቲስቲክስ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች በቅድሚያ መጥቀሱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: ለዚህ ተግባር የተቋቋመው የአሁኑ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣ "የጠቅላይ ስታቲስቲክስ ጽሕፈት ቤት" ተብሎ ከተመሰረተበት ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ የሀገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ በየጊዜው አቅም በፈቀደ መጠን የተቻለውን ሲያከናውን መቆየቱ ይታወቃል:: በመሆኑም በርካታ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የሥነ ሕዝብ ጥናቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ከማካሄዱም በላይ በ1976 የመጀመሪያውን ዙር የሕዝብና ቤት ቆጠራ እንደዚሁም በ1987 የሁለተኛውን ዙር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባራት በአገር አቀፍ ደረጃ አካሂዶ ውጤቱን ለተጠቃሚዎች አሠራጭቷል::

የአንድን ሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ፣ በእነዚህ ፖሊሲዎች ላይ ተመስርቶ የልማት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ የልማት ዕቅዶቹ በተግባር ላይ ሲውሉም ውጤታቸውን ለመከታተልና ለመገምገም፣ እንደዚሁም የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች ለማካሄድ ብሎም እያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ለሀገር ሀብት ውጤት (GDP) የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት ወቅታዊና አስተማማኝ ስታትስቲካዊ መረጃዎች ያስፈልጋሉ::

ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ዲሞግራፊያዊ ሁኔታዎችን ሊያመለክቱ የሚችሉ አሀዛዊ መግለጫዎች ናቸው::

የአሠራር ሂደቱም በሣይንሳዊ ዘዴ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማቀነባበር፣ የመተንተኝ ብሎም ውጤቱን ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባርን ያካትታል፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ከላይ ለተጠቀሱት አጠቃላይ ዓላማዎች መሟላት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ጥናቶችን በማካሄድ እንደዚሁም በጥናቶቹ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማቀነባበርና በመተንተን ያዘጋጃቸውና ያሰራጫቸው ሪፖርቶች ለልዩ ልዩ ሥራዎች ተጨባጭ መነሻ በመሆን ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እየዋሉም ነው፡፡

የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ፣ ቅንብርና ጥንቅር ሥራ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ በመሆኑ ተግባሩ የሚከናወነው በሙያው ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ባካበቱ ባለሙያዎች በተለይም ባለንበት ዘመን በዘመናዊ መሣሪያዎች ጭምር በመታገዝ ነው፡፡ የስታቲስቲክስ መረጃ ወቅታዊ፣ አስተማማኝ፣ ደረጃውን የጠበቀና በሚፈለገው ዓይነትና በተለያዩ የአስተዳደር እርከን ተለይቶ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ይህ መግለጫ አጠቃላይ ጉዳዮችን ማለትም የስታቲስቲክስ መረጃ ጥቅምና አስፈላጊነት፣ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ የጥናቶች አፈጻፀም ቅደም ተከተል፣ የስታቲስቲክስ መረጃ ማሠራጫ ዘዴዎች እንደዚሁም የ1990 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻፀም፣ በማጠቃለያው ክፍልም ከመ/ቤቱ ዕቅድ አፈፃጸም አንፃር ከመረጃ ሰጪዎች እንዲሁም ከሕብረተሰቡ የሚጠበቅ ትብብርን የሚገልጽ ይሆናል፡፡

## 2. የስታቲስቲክስ መረጃዎች ጥቅምና አስፈላጊነት

2.1. የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል/ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የሚያገለግሉ የመነሻ መረጃዎችን ያስገኛሉ ፣

2.2. በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሕብረተሰቡን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ የልማት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት፣ ዕቅዶቹ ሲተገበሩ አፈጻጸማቸውን ለመከታተልና ለመገምገም ያገለግላሉ ፣

2.3. በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በዲሞግራፊያዊ መስኮች አዲስ ወይም ቀጣይ ጥናቶችን ወይም ምርምሮችን ለማካሄድ መነሻ ወይም መሠረት በመሆን ያገለግላሉ ፣

2.4. በተለያዩ ጊዜያቶችና ቦታዎች የነበሩትን ወይም ያሉትን ክስተቶች ለማወዳደርና ለማነጻጸር ብሎም የወደፊቱን ለመተንበይ ይጠቅማሉ ፣

2.5. በክልሎች መሀል የተቀራረበ ዕድገት ለማስፈን ለሚደረጉ ጥረቶች የሚረዱ በአሃዝ የተደገፉ መረጃዎችን ለማቅረብ ይጠቅማሉ ፣

2.6. የግል ባለሀብቶች መዋዕለ-ንዋያቸውን በየትኛው የሥራ ዘርፍ፣ ምን ያህል፣ የት ቦታ ኢንቨስት ቢያደርጉ ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአመልካችነትና በመነሻነት ያገለግላሉ ፣

2.7. የአንድን አገር ሕዝብ ብዛትና ስርጭት በዕድሜ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በብሔረሰብ፣ በጤና ሁኔታ፣ በትምህርት ደረጃ፣ ....ወዘተ ለፖሊሲ ቀረጻ፣ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ ለጥናትና ለምርምር እንደዚሁም ለአስተዳደር ጉዳዮች እና የምርጫ ሂደት ለማስፈጸም ያገለግላሉ።

## 3. የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የስታቲስቲክስ መረጃዎችን አጠናቅሮ፣ ተንትኖና በተለያየ መልክ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት በቅድሚያ መረጃዎችን የመሰብሰብ ተግባር መከናወን ይኖርበታል። ይህን ተግባር ማከናወን ከሚያስችሉ ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

## 3.1. አጠቃላይ ቆጠራዎች (CENSUSES)

ይህ ጥናት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ከሚመለከታቸው ሁሉ፣ ከእያንዳንዱ በነፍስ ወከፍ የተፈለጉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያበቃ ዘዴ ነው።

- አጠቃላይ የህዝብና ቤት ቆጠራ ስለ ሕዝብ ብዛት፣ በፆታ፣ በዕድሜና በሕዝብ ብዛት ስለደረሱ ለውጦች (ሞት፣ ልደትና ፍልሰት) ስለ ትምህርት ችሎታ፣ ስለቋንቋ፣ ስለ ቤቶች ሁኔታ....ወዘተ፣ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ቆጠራ ስለ ኢንዱስትሪ ምርት ውጤትና የሠራተኞች ሁኔታ፣ ስለ ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አጠቃቀም....ወዘተ፣

- አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ስለ እርሻ ውጤትና የመሬት አጠቃቀም፣ ስለ ቤት እንስሳት፣ በገጠሩ በግብርና ስለሚተዳደረው ሕዝብ ብዛት... ወዘተ ስለ አጠቃላይ ቆጠራ በምሳሌነት ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው።

- አጠቃላይ ቆጠራ በነፍስ ወከፍ ከሁሉም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ትኩረት ስለሚያደርግ ከፍተኛ የሰው ኃይልና ወጪን የሚጠይቅ፣ እንደዚሁም መረጃዎችን ሰብስቦና አቀነባብሮ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ጊዜ የሚወስድ ተግባር በመሆኑ አጠቃላይ ቆጠራ በየአጭር ጊዜው የሚካሄድ ሳይሆን በየአምስቱ ወይም በየአስሩ ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ነው።

## 3.2. የናሙና ጥናት (Sample Survey)

ይህ ጥናት፣ ጥናቱ ከሚመለከታቸው የተወሰኑትን በመምረጥና በማጥናት የተገኙትን መረጃዎች በመጠቀም በአጠቃላይ፣ ጥናቱ ስለሚመከታቸው ሁሉ አስተያየት ለመስጠት ብቁ የሚያደርግ ሳይንሳዊ ዘዴ ነው።

ለምሣሌ፣ የቤተሰብ ገቢና የገቢን አጠቃቀም ሁኔታ ለማጥናት በነፍስ ወከፍ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ይህን ዓይነት መረጃ ለማጠናቀር ከባድና አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉንም ቤተሰቦች ከማጥናት ይልቅ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ከጠቅላላው ቤተሰብ ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥና እነሱን በጥናቱ በመሸፈን ስለ ጠቅላላው የቤተሰብ የገቢ አጠቃቀም ሁኔታ ግምገማ ለማድረግ የከፊል ወይም የናሙና ጥናት ዓይነተኛ ዘዴ ነው።

## 3.3 የአስተዳደር መዛግብት (Adminstrative Records)

መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በአለባቸው ኃላፊነትና ተግባር መሠረት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን ለማስረዳት የሚቻለው ይህንኑ የሚያመለክት መዛግብት ሲይዙ ብቻ ነው፡፡ ድርጅቶች ስለሚያመርቱት ምርት ብዛትና ዓይነት፣ ስለሚሰጡት ለአገልግሎት ብዛትና ዓይነት፣ ስለሠራተኞች ሁኔታ፣ ስለተፈጥሮ ሐብት....ወዘተ የሚገልጹ መዛግብት መያዝ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ስለ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማቅረብ ይህ ዘዴ ዓይነተኛና አስተማማኝ መሣሪያ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሥራ የድርጅቶችንና የመሥሪያ ቤቶችን ግዴታና ኃላፊነት የተጠናከረና የተሟላ የመዝገብ አያያዝ ዕውቀትና ልምድ ይጠይቃል፡፡

## 3.4 የማያቋርጥ ምዝገባ ሥርዓት Continous Registration System)

ይህ ተግባር በተወሰነ ወቅት (በአብዛኛው ጊዜ በዓመት) የሚከሰቱትን ክንዋኔዎች ለምሣሌም ልደትና ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ፣ ፍልሰትን ተከታትሎ የመመዝገብ ተግባር ነው፡፡

# 4. የስታቲስቲክስ ጥናቶች አፈጻጸም ቅደም ተከተል

የስታቲስቲክስን ጥናቶች በተለያዩ ዘዴዎች አካሂዶ ዳር ለማድረስ አራት የተያያዙ የአሠራር ሂደቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም፡-

## 4.1. የዝግጅት ወቅት

ሀ. የጥናቱ ዓላማ ፣ ጥቅምና አስፈላጊነት እንደዚሁም ጥናቱን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና የበጀት ፍላጎት የሚያመለክት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፣

ለ. የጥናቶቹን ዓላማዎች ለሚሟላት መሰብሰብ የሚኖርባቸውን የመረጃዎች ዓይነት መወሰኝ፣

ሐ. የተፈለጉ መረጃዎች ከምን/ከየት ሊገኙ እንደሚችሉ ማወቅ /ከቤተሰብ ፣ ከግለሰብ፣ ከድርጅት ፣ ከመሥሪያ ቤት፣.... ወዘተ፣

መ. መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን ሜቶዶሎጂ መቀየስ፣

ሠ. ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ዶኩመንቶች ማለትም መጠይቆች መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ቅጾች ማዘጋጀት ፤

ረ. ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በቅድሚያ አውቆ ተገቢ ስልት መቀየስ እንዲቻል የሙከራ ጥናት ማካሄድ፣

ሰ. ለጥናቱ የሚያስፈልግ የሎጅስቲክስና የማቴሪያል ፍላጎት ማሟላት

ሸ. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን የመመልመል፣ የማሠልጠንና የማስማራት ተግባራትን ማከናወን፣

## 4.2 መረጃ ከመስክ መሰብሰብ

ሀ. ተፈላጊ መረጃዎች ጥናቱ እንዲካሄድባቸው ከተመረጡ ቆጠራ ቦታዎች (አካባቢዎች) ወይም ከአስተዳደር መዛግብት በተቀየሱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ከቤተሰብ ወይም ከድርጅቶች የስታቲስቲክስ መረጃ መሰብሰብ፣

ለ. ከመስክ በገጠር ወይም በከተማ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ወይም ከተሰበሰበ በኋላ የመረጃውን ጥራትና ትክክለኛነት መቆጣጠር፣

ሐ. መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆችና ቅጾች ትክክለኛነታቸው በተዋረድ ተረጋግጦ ከመስክ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት እንዲተላለፉ ማድረግ፣

## 4.3 መረጃ ቅንብር

ሀ. ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ኮምፒውተር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ለቅንብር በሚያመች ሁኔታ የኤዲቲንግና የኮዲንግ ሥራ ማከናወን፣

ለ. አሀዛዊ መረጃውን ኮምፒውተር ውስጥ ማስገባት፣

ሐ. በኮምፒውተር አማካኝነት አሃዛዊ መረጃውን ኤዲት በማድረግ (በማረም) እና የማገናዘብ ሥራ ማከናወን፣

መ. ለሪፖርት ዝግጅትና ትንተና የሚያስፈልጉ ሠንጠረዦች ማዘጋጀት ፤

ሠ. በተዘጋጀው የሠንጠረዥ ዕቅድ (Tabulation Plan) መሠረት የኮምፒውተር ፕሮግራም በመጻፍ የመረጃ ቅንብሮችን መሥራት፣

## 4.4. ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ስርጭት

ሀ. በሠንጠረዥ የተዘጋጁትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የጥናቱን ግኝት (Findings) በመገምገምና በመተንተን ዝርዝር ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ለ. የተዘጋጁትን ሪፖርቶች በበቂ ቅጅዎች በማተም ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፣

ሐ. የጥናቱን ውጤት ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅና ለማብራራት እንደአስፈላጊነቱ ሴሚናሮችን /አውደ ጥናቶችን የማዘጋጀት ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 5. የስታቲስቲክስ መረጃ ማሠራጫ ዘዴዎች

መረጃዎች ለአጠቃቀም በሚያመች ሁኔታ በተለያዩ የአስተዳደር እረከኖች ከተዘጋጁ በኋላ፡-

5.1 የመረጃዎቹ ከፍተኛ ተጠቃሚ ለሆኑ መሥሪያ ቤቶችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በነፃ ዕደላ ይደረጋል፣

5.2 በቤተ መጻሕፍት ውስጥ በቂ ቅጅዎች በማስቀመጥና መረጃ ፈላጊዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ግልጋሎት ይሰጣል፣

5.3 እንደ አስፈላጊነቱ በኮምፒውተር ዲስኬቶች፣ በቴፖች፣ በሌሎች ኢሌክትሮኒክ ሚዲያዎች... ወዘተ የጥናት ውጤቶችን ሆነ የስታቲስቲክስ ሠንጠረዦችን መረጃ ተጠቃሚዎች እንዲወስዱ ይደረጋል፣

5.4 የሀገር ውስጥና የውጭ አገር መረጃ ጠያቂዎች የፖስታ ወጪና የሪፖርቶችን ዋጋ እንዲሸፍኑ/እንዲከፍሉ በማድረግ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ

5.5 የመረጃ ሥርጭት ሴሚናር (Dessimination Seminar) በማካሄድ በጥናቶችና በቆጠራዎች የተገኙ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ፡፡

5.6 በሽያጭ ለመረጃ ፈላጊዎች በግዥ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

# 6. የማ.ስ.ባ. የ1990 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም

## 6.1 የጥናቶች ዓይነትና የአፈጻጸም ደረጃ

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በ1990 በጀት ዓመት ለስታቲስቲክስ መረጃ ሀብት መዳበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ጥናቶችን በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በማጠቃለል አካሂዷል:: እነዚህም:- የዘመኑን የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የግብርና ናሙና ጥናት፣ አምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የጤናና የአመጋገብ ጥናት፣ የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ የሙከራ ጥናት ሲሆኑ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትም በተናጠል ለማካሄድ ታቅዶ ተግባራዊ ሆኗል:: በተጨማሪም በ1989 ዓ.ም የተካሄዱ ጥናቶች ሪፖርት ዝግጅትና ሥርጭት በዚሁ ዓመት ተጠናቋል::

ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች ከማካሄድና ከማጠናቀቅ በተጨማሪ በሶማሌ ብሔራዊ ክልል በ1989 በጀት ዓመት ለማካሄድ ታቅዶ የነበረው ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ባጋጠሙ ልዩ ልዩ ችግሮች ምክንያት ማካሄድ ባለመቻሉ ወደ 1990 የተሻገረው መረጃ የመሰብሰብ ተግባር በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሩብ ዓመት ውስጥ እስከ ህዳር መጀመሪያ ሣምንት ድረስ ተካሂዶ በመጠናቀቁ ውጤቱ በጥር ወር 1990 ዓ.ም ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል:: እንደዚሁም በ1987 በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተሰበሰበው መረጃ ቀጣይ የትንተና ሪፖርት ዝግጅት በመከናወን ላይ ይገኛል::

በዕቅድ ከተያዙትና በየበጀት ዓመቱ ከሚካሄዱት መደበኛ ጥናቶች በተጨማሪ በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ክልል አቀፍ ወይም ሀገር አቀፍ ይዘት ያላቸው ጥናቶች የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እንዲያጠናላቸው ጥያቄ ሲቀርብ ጥናቱን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ወጪ፣ ሜቶዶሎጂ፣ የጥናቱ ይዘት፣ ..... ወዘተ በተመለከተ በሚደረስበት ስምምነት መሠረት ጥያቄዎችን ተቀብሎ ጥናቶቹን አካሂዷል:: በዚሁ መሠረት በዚህ በጀት ዓመት መሥሪያ ቤቱ ከሐረሪ ብሔራዊ ክልል ግብርና ቢሮ ስለ ብሔራዊ ክልሉ አጠቃላይ የግብርና እንቅስቃሴ እና ከማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ደግሞ የማዳበሪያ አጠቃቀም መሠረታዊ መረጃዎች ጥናት ተቀብሎ አጥንቷል::

## 6.1.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራና ሌሎች የሥነ-ሕዝብ ነክ ጥናቶችን በተመለከተ

ሀ. በሶማሌ ብሔራዊ ክልል ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራን በሚመለከት የተከናወኑ ሥራዎች

- የቆጠራ ቅደመ ዝግጅት ሥራዎች ማለትም የቆጠራውን ስልት መንደፍ፣ መጠይቆችና፣ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያዎችን የማዘጋጀትና ማተም እንደዚሁም አስፈላጊ የመሥክ መገልገያ መሣሪያዎች የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል።

- በብሔራዊ ክልሉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማካሄድ እንዲያገለግል በሁሉም ወረዳዎች የቀበሌዎች፣ የመንደሮችና የቤተሰቦች ምዝገባ ተካሂዷል። ምዝገባው የተካሄደው በመሥሪያ ቤቱ ነባር ሠራተኞች አማካኝነት በቡድን በማደራጀት ነበር።

- በተካሄደው የቤተሰብ ምዝገባ የቤተሰብ አባላት ዝርዝር በፆታ በመለየት ተሰብስቧል። የምዝገባው ውጤትም በዋናው መ/ቤት በኮምፒውተር ተቀርጾ አስፈላጊ መረጃ ተጠናቅሯል።

- የቆጣሪዎች ምልመላና ቅጥር በአጠቃላይ የተፈጸመው በአብዛኛው ከክልሉ ነው። ለቆጠራው ሥራ በተቆጣጣሪነት የተሰማሩት ደግሞ በአብዛኛው የመሥሪያ ቤቱ ነባር መረጃ ሰብሳቢዎች ናቸው። የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ምልመላና ሥልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ መስክ እንዲሰማሩ ተደርጎ የቆጠራውን ሥራ አከናውነዋል። በዚህ ቆጠራ ሥራ 3381 ቆጣሪዎች፣ 3381 መንገድ መሪዎችና ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው አስተርጓሚዎች ተሰማርተው ሥራውን አከናውነዋል። እንደዚሁም ከዋናው መ/ቤት 128 የጽ/ቤት ሠራተኞች በተለያዩ የሥራ ኃላፊነት፥ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ 824 በቆጠራ የዝግጅት ሥራዎችና በተቆጣጣሪነት ተሰማርተው የቆጠራውን ሥራ በሚጠበቀው ሁኔታ እንዲፈጸም አድርገዋል።

- ለቆጠራው ሥራ ከባለሥልጣኑ መ/ቤት እና ከሌሎች መ/ቤቶች የተገኙ 128 ተሽከርካሪዎች ተሰማርተዋል።

- ሕብረተሰቡ የቆጠራውን አስፈላጊነትና ጥቅም ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ እንዲተባበር የትምህርትና የቅስቀሳ ተግባር በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በፖስተር ተከናውኗል። ለዚሁ ተግባር በአማርኛና በሶማሊኛ ቋንቋዎች የትምህርትና የቅስቀሣ ጽሑፎች ከመዘጋጀታቸውም በተጨማሪ ሦስት ዓይነት የቆጠራ ትምህርትና ቅስቀሣ ፖስተሮች ተመርጠውና ታትመው በየወረዳው እንዲበተኑ ተደርገዋል።

- የቆጠራውን ሥራ ለማስፈጸም የማዕከላዊ፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ቆጠራ ኮሚሽኖችና የቀበሌ የቆጠራ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡

- የመከላከያ ሠራዊት፣ የሀገር ሽማግሌዎች ፣ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተውጣጥተው በጥምር ኮሚቴ የተደራጁ የቆጠራውን ሥራ እንዲያስተባብሩ ተደርጓል፡፡

- በቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደ ዋናው መ/ቤት በማሰባሰብ ለኮምፒውተር ቅንብር በሚያመች መልኩ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራዎች ተከናውዋል፡፡

- መረጃውን በኮምፒውተር ውስጥ የማስገባትና የተለያዩ ሠንጠረዦች ዝግጅት ተከናውነዋል፡፡

- የመረጃው በኮምፒውተር የመቀነባበሩ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የቆጠራው ውጤት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

ለ. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ</u>

የሁሉም ብሔራዊ ክልሎችና አስተዳደሮች የቆጠራ ስታቲስቲካል ሪፖርቶች ከወጡ በኋላ ተመሳሳይ ስታቲስቲካል ሪፖርትም በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ የህትመት ሥራው ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ እንደዚሁም የአብዛኛው ብሔራዊ ክልሎችና አስተዳደሮች ረቂቅ አናሊቲካል ሪፖርት የተጠናቀቀ ሲሆን ከእነዚህ መሐል የትግራይ ሪፖርት በሕትመት ላይ ይገኛል፡፡

ሐ. <u>የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ የሙከራ ጥናት በተመለከተ፣</u>
<u>የጥናቱ ዓላማዎች:-</u>

- ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚቋቋመው የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በቅድሚያ ለማወቅ፣

- ምዝገባው ከሕግና ከአስተዳደር አንፃር እንደዚሁም በመረጃ ማቀናጀትና በሜቶዶሎጂ ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቅድሚያ ለማወቅ፣

- ሕብረተሰቡ የምዝገባውን አስፈላጊነትና ጥቅም እንዲረዳ ለማድረግ፣

- የሕዝቡን የጾታ፣ የዕድሜና የጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች በመሰብሰብ የየዓመቱን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የፍልሰት መጠን ለማጥናት፣

- ከቫይታል ምዝገባ በተጨማሪ ወደፊት የሕዝብ ምዝገባ ሥርዓት የሚቋቋምበትን መንገድ ለማጥናት ...... ወዘተ ናቸው።

በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችም በሕብረተሰቡ ውስጥ ስለተከሰተው ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻ፣ ፍቺና ፍልሰት መረጃዎች እንደዚሁም የጾታና የዕድሜ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

መ. የጤናና አመጋገብ ጥናትን በተመለከተ

የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ የሕዝቡን የጤንነትና የአመጋገብ ሁኔታ ለማሻሻል በአገር አቀፍ በክልልና በዞን ደረጃ እንዲሁም በገጠርና በከተማ ለሚታቀዱትና ለሚቀየሱት የጤናና አመጋገብ ፕሮጀክቶች መሠረት የሚሆንና እንደዚሁም የሕዝቡን የጤንነትና የአመጋገብ ሁኔታ ለማሻሻል የሚዘረጉትን ፕሮግራሞች ሂደት ለመከታተልና ለመገምገም የሚረዱ መረጃዎችን ለማስገኘት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- በተለያዩ አካባቢዎች የበሽታዎች ዓይነትና ሥርጭት እንዲሁም የአደጋዎችን ሥርጭት ለማሳየት የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣

- ሰዎች በታመሙ ጊዜ የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት የት እንደሚሄዱ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ለማወቅና ታመው የሕክምና ዕርዳታ ያላገኙበትን ምክንያት ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማግኘት፣

- ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ስጪ ድርጅቶችን በሚመለከት ሕዝቡ ያለውን አስተያየትና የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚመጣጠን ማሳየት፣

- ወላድ ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ በምን ዓይነት የማዋለጃ አገልግሎት እንደሚጠቀሙ ለማወቅና ዘመናዊ የሕክምና ክትትል የሚያደርጉ ስለመሆናቸው የሚያመለክት መረጃ ለመሰብሰብ፣

- የአመጋገብ ችግሮችን ለማወቅና እነዚህንም ችግሮች ለማሻሻል የሚያስችሉ መርሀ ግብሮችን ለመቅረጽ መሠረት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣

- የአመጋገብ ችግር ጎልቶ የሚታይባቸውን አካባቢዎች/የሕብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ በማወቅ ለሚመለከታቸው የዕቅድ አዘጋጆችና አስፈጻሚ ዘርፎች ማኛ ለምን የአመጋገብና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ ችግር እንዳለበት ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣

- ነፍሰጡር ሴቶች፣ ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ከትባት የሚያገኙ ወይም የማያገኙ ስለመሆናቸው የሚያመለክቱ መረጃዎች ማግኘት፣

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆናቸው ልጆች ስለጡት መጥባት መረጃ መሰብሰብ፣

- በአመጋገብ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የቤተሰብ አባላት/ የሚያጠቡ እናቶች፣ ነፍሰጡር ሴቶችና ከ5 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆች/ ተጨማሪ ምግብ ያገኙ ወይም አያገኙ እንደሆነ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ::

- በሚሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና መርሀ ግብሮች በሕብረተሰቡ የአመጋገብና የጤንነት አቋም ላይ ያስከተሉትን ውጤቶች ለመከታተልና ለመገመገም ናቸው::

<u>በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች</u>

በጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው::

- የተወሰኑ የማኅበራዊና የሥነ-ሕዝብ ሁኔታዎች፣

- ጥናቱ ከሚካሄድበት ቀን ጀምሮ ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች፣

- በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት የዘወትር ተግባር ስለማቋረጥ፣

- ጥናቱ ከሚካሄድበት ቀን ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ አደጋዎች፣

- ባለፉት 12 ወራት በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት በቤተሰቡ አባላት ላይ ጉዳት መድረሱ አለመድረሱ፣

- ባለፉት 12 ወራት ጉዳት የደረሰባቸው አባላት የሕክምና እርዳታ የማግኘት ሁኔታና ስለዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ያላቸው አመለካከት፣

- ወላድ እናቶች ሲወልዱ ማን እንዳዋለዳቸውና በእርግዝና ወቅት ዘመናዊ ሕክምናና ክትባት ስለመውሰዳቸው፣

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆናቸው ልጆች ክትባትና ቫይታሚን እንክብሎች ስለመወሰዳቸው፣

- ባለፉት 14 ቀናት ሕፃናት ተቅማጥ፣ ተውከትና ሳል ስለመታመማቸውና ታመው ምን እንደተሰጣቸው፣

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆናቸው ልጆች ጡት የማጥባት ሁኔታ፣

- በአመጋገብ በኩል ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የቤተሰብ አባላት ተጨማሪ ምግብ ስለመመገባቸው፣

- ዕድሜያቸው ከ3-59 ወራት ለሆኑ ልጆች የቁመትና ክብደት ልኬቶች፣

## 6.1.2 የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታትስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች

### ሀ. የግብርና ስታትስቲክስ ጥናቶችን በተመለከተ

### i) የሰብል ትንበያ ጥናት

- የሰብል ትንበያ ጥናት ዓላማዎች

የሰብል ትንበያ ጥናት ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የሀገሪቱን ክልሎች በሙሉ በሚሸፍኑ በናሙና በተመረጡ ቆጠራ ቦታዎች የሚካሄድ ሲሆን የጥናቱ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- በምርት ዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን ምርት በመገምገም በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የምርት መጠን ከወዲሁ በመገመት ወደፊት በሀገሪቱ ሊመረት የሚችለውን የምርት መጠን ለመተንበይ (Crop Production forecast)፣

- በምርት ዓመቱ ትርፍ ምርት ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርት እጥረት ሊያጋጥማቸው የሚችሉትን ክልሎችና ዞኖች መለየት የሚያስችሉ የትንበያ መረጃዎችን ማቅረብ ናቸው፡፡

- **በሰብል ትንበያ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት**

ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናቱን ዓላማዎች ለማሟላት የሚከተሉት የመረጃ ዓይነቶች በተጨባጭና (Objective) በቃለ መጠይቅ (Subjective) የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በመጠቀም ጥናቱ ከሚካሄድባቸው ቆጠራ ቦታዎች ይሰበሰባሉ፡፡

- የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
- የሚጠበቀው የምርታማነት ለውጥ ከአለፈው ዓመት ምርት በሰብል ዓይነት ጋር ሲወዳደር በመቶኛ ናቸው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶ ታትሟል፡፡

## ii) የግብርና ናሙና ጥናት

- **የግብርና ናሙና ጥናት ዓላማዎች**

ሀገሪቱ በየዓመቱ በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ለምታዘጋጀው የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ፖሊሲ እንደዚሁም የልማት ዕቅዶች ለማዘጋጀት የሚረዱ መረጃዎች ለማስገኘት ሲሆን ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሀገሪቱ በዓመቱ የተመረተውን አጠቃላይ የሰብል ምርት ለማወቅ፣ በክልሎችና በዞኖች ደረጃ ያለውን የምርት ሁኔታ ለማወቅ፣ ለማወዳደርና ለማነጻጸር የሚያስችል መረጃዎች ለማግኘት፣

- ከአንድ ሄክታር ላይ የሚገኘው ምርትና ምርታማነት ምን ያህል እንደሆነ እንደዚሁም በክልሎችና በዞኖች መሐል ያለውን የምርትና የምርታማነት ልዩነት ለማወዳደርና ለማነጻጸርም የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፣

- ከዓመት ወደ ዓመት በሀገር ደረጃ የታረሰ መሬት ስፋትና ያለውን የምርት መጠን በመኸርና በበልግ ወቅት በመለየት በሰብል ዓይነት የታየውን ለውጥ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፣

- የእርሻ ሥራን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ጥቅም ላይ የዋለ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና የፀረ-ሰብል መድሐኒት ዓይነት እንደዚሁም የመስኖ አጠቃቀም .... ወዘተ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፣

- በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ማለትም በሰብል ስለተያዘ መሬት፣ እጸሪ መሬት፣ በግጦሽ የተያዘ መሬት፣ በደን የተሸፈነ መሬት.... ወዘተ የሚያሳዩ መረጃዎች ለማግኘት፣

- በሀገሪቱ ያሉትን የቤት እንስሳት በተመለከተ ብዛታቸውን በዓይነት ፣ በዕድሜና በጾታ እንደዚሁም ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ለመገምገም የሚያበቁ መረጃዎችን ለማግኘት ናቸው::

- <u>በግብርና ናሙና ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

የዚህ ጥናት መኸር ወቅት መረጃ (የሰብል ምርት ግብዓቶች ጭምር) ከመስከረም ወር መጀመሪያ እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ የሚሰበሰብ ሲሆን የበልግ ወቅት መረጃ ደግሞ በግንቦት ወር ውስጥ ይሰበሰባል:: የዓመቱ የግብርና ጥናት አካል የሆኑት የቤት እንስሳት፣ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት የሚያሳይ መረጃም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በየካቲት ወር ተሰብስበዋል:: በንዑስ ጥናቶቹ አማካይነት ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሐል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የታረሰ መሬት ስፋትና አማካይ የምርት መጠን በሰብል ዓይነት፣
- የመሬት አጠቃቀም (Land Utilization)
- የዘር ዓይነት አጠቃቀም፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም በዓይነት ፣ በመጠንና በዋጋ፣ የፀረ ሰብል ተባይና አረም ማጥፊያ አጠቃቀም እና የቋሚ ሰብል እግር ብዛት፣
- የቤት እንስሳትና የዶሮ ብዛት በዓይነት፣ በዕድሜ ፣ በጾታና በሚሰጡት የጥቅም ዓይነት ፣
- ስለ ንብ ቀፎዎች ዓይነት፣ ብዛትና የማር ምርት መጠን የሚያሳይ መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

የዚህ ጥናት ውጤት በአራት ዓይነት ሪፖርቶች ማለትም የታረሰ መሬት ስፋትና የሰብል ምርት መጠን፣ የእርሻ ሥራ ሁኔታ፣ የመሬት አጠቃቀም ዝግጁ ሆኗል:: እንደዚሁም የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ቀፎዎች፣ የበልግ ወቅት፣ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ሪፖርቶች እየተዘጋጁ ናቸው::

## ለ. <u>የዋጋ ጥናቶችን በተመለከተ</u>

የዋጋ ጥናት በየዓመቱና በየወሩ በገጠርና በከተማ ይካሄዳል:: በዚህ ጥናት አማካይነት የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: እነዚህን መረጃዎች መሠረት

በማድረግም በየወሩ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶች በሀገር አቀፍ በገጠርና በከተማ/ከተሞች ደረጃ ይዘጋጃሉ፡፡

## i) የአምራች ዋጋ ጥናት

### • የአምራች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የአምራች ዋጋ ጥናት በገጠር በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ አበይት ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፖሊሲ አውጪዎች ስለ እርሻ ውጤቶች ምርትና ስርጭት አስመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚረዱ መረጃዎች፣
- ገበሬዎች በአምራች ደረጃ ለእርሻ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን የዋጋ መጠን ለማጥናት መሠረት የሆኑ መረጃዎች፣
- የምርት ጠቅላላ ዋጋንና የሀገር ሐብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች፣
- የእርሻ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋን የምርት መጠን መመዘኛ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው፡፡

### • በአምራች ዋጋ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ለአምራች ዋጋ ጥናት በገጠር ከተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የእህል፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ፣ የቅመማ ቅመም ፣ የወተትና የወተት ተዋጽኦ፣ እንቁላል፣ የቁም ከብቶች፣......ወዘተ መረጃዎችን ያጠቃልላል፡፡

## ii) የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

### • የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠርና በከተማ በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የችርቻሮ ዋጋ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማወቅ፣

- በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለመገምገም፣
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ምርትና ስርጭትን በሚመለከት ፖሊሲ አውጭዎች ውሣኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ መነሻ መረጃዎች ለማግኘት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሐብት ውጤትን ለማስላት እንደዚሁም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎች ለመሰብሰብ ናቸው።

- <u>በችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠርና በከተማ ከተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች በዋና ዋና የመገበያያ ቦታዎች የእርሻና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከግል ነጋዴዎች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትንባሆ ፣ የልብስ፣ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪያዎች፣ የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ የሕክምና መድኃኒት፣ የመጓጓዣ፣ የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች የሆቴል ምግብና የአልጋ ዋጋ፣ .... ወዘተ መረጃዎች ናቸው። በእነዚህ ዋጋዎች ጥናት ላይ በመመርኮዝ በየወሩ የአዲስ አበባ፣ የከተሞች፣ የገጠርና የአገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶች (ሸማቾች ለተወሰኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚከፍሉትን አማካይ የዋጋ ለውጥ ለማየት የሚያገለግል አሀዝ ነው።) እየተዘጋጁ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

## ሐ. <u>የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት</u>

ይህ ጥናት የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለመከታተል ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

- <u>የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት ዓላማዎች</u>

የጥናቱ ዓላማዎች በርካታ ሲሆኑ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በሀገሪቱ ውስጥ ለሚታየው የድህነት ሁኔታ መሠረታዊና ጠቋሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንደዚሁም ወደፊት የሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ለመከታተልና ለመገምገም፣
- ድህነትን ለመቀነስና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እንዲቻል በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረ ዘላቂ መረጃዎች ለማቅረብ ናቸው።
- የሀገሪቱን የድህነት መስመር (Poverty line) ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

- **በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት**

በጥናቱ የሚሰበሰቡት የመረጃዎች ዓይነት የሚከተሉትን ጉዳዮች/ሁኔታዎች ያካተቱ ናቸው። እነዚህም፦

- የቤተሰብ የጤናና የትምህርት ሁኔታ፣
- ቤተሰቡ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች ዓይነት ማለትም የማገዶ፣ የመጠጥ ውሃና አቅርቦት፣ የመብራት ዓይነት፣ የመጸዳጃ ዓይነት፣ ....ወዘተ፣
- ስለ ቤተሰቡ ቋሚ ንብረቶች፣
- ስለ አካባቢው የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና የአቅርቦት ሁኔታ፣
- የሕፃናት ክብደት፣ ቁመትና የጤና ሁኔታ ፣
- ስለ ቤተሰብዎ መደበኛ ወርሃዊ ገቢና ወጪ መጠንና ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ይኸው የገቢና የወጪ መጠን ያሳየው ለውጥ... ወዘተ ናቸው።

*መ.* ***የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትን በተመለከተ***

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በኢኮኖሚው ዘርፍ በየዓመቱ ከሚያከናውናቸው ዓበይት ጥናቶች አንዱ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ነው። የትላልቅና የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የሚባለው በአማካይ አሥርና ከአሥር በላይ ሠራተኞችን የሚያስማራ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፣ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርት ፋብሪካን ሁሉ የሚያካትት ነው። ለምሣሌ፣ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የጫማ መምረቻ ፣ የዳቦ መጋገሪያ፣ የእንጨት መሠንጠቂያና የቤትና የቢሮ ዕቃ ማምረቻ የቆዳ ፋብሪካ፣ የዱቄት ማምረቻ ፣ ወዘተ... የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

- ***የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣***

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አውጭዎች ፣ ኢንቨስተሮች እንዲሁም ተመራማሪዎች ለመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪ ዓይነትና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያሠማራውን የሰው ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለአገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት፣
- ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ከውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር ለመሰብሰብ፣
- የዘርፉን ልዩ ልዩ ችግሮች በመሰብሰብና በመተንተን ለፖሊሲ አውጭዎች የመነሻ መረጃ ማቅረብ፣ የዚህ ጥናት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

## በጥናቱ የተሰበሰቡ የመረጃዎች ዓይነቶች፣

በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የተሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የፋብሪካዎች ብዛት፣
- የተከፈለ ካፒታል (PAID-UP CAPITAL) መጠን፣
- የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም (የባለቤትነት ዓይነት፣
- በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት በፆታና በሙያ ዓይነት፣
- ለሠራተኞች የተከፈለ ዓመታዊ ደመወዝ በሙያ ዓይነት፣
- የምርት ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ዓይነት መጠንና ዋጋ፣
- ልዩ ልዩ ከምርት ሂደቱ ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ውጪዎች፣
- ፋብሪካው የሚጠቀምባቸው የቋሚ ንብረት ዓይነትና ዋጋ፣
- ዓመታዊ የመዋዕለ ንዋይ መጠን (Annual Investment)፣
- ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ የማምረት ችሎታው መጠን፣
- የፋብሪካው ልዩ ልዩ ችግሮች፣ ወዘተ...ናቸው።

የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በየዓመቱ የሚካሄደው የጥናቱ ዓመት ካለፈ ከ3-6 ወራት በኋላ ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት በተለይ ትላልቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ሒሳባቸውን ዘግተው ቢያንስ ጊዜያዊ የሒሳብ ማጠቃለያ ሠርተው መረጃ ለመስጠት የምርት ዓመቱ ካለቀ በኋላ የተወሰነ ወራት ስለሚያስፈልጋቸው ነው። በመሆኑም የ1989 በጀት ዓመት መረጃን የሚያሣይ ጥናት ግንቦት 1990 የተካሄደ ሲሆን መረጃው በመቀነባበር ላይ ነው።

በማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ሌሎች የተካሄዱ ጥናቶች ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል የአነስተኛ ፣ የጎጆና የዕደ ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ናቸው። በዚህ ረገድም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከ1989 በጀት ዓመት ጀምሮ በየሦስት ዓመቱ እነዚህን ጥናቶች ለማከናወን ዕቅድ ይዞአል። ስለሆነም በ1989 ዓ.ም. የእነዚህ ጥናቶች መረጃ ተሰብስቦ፣ የቅንብርና የትንተናው ሥራው ተጠናቆ በ1990 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

## 7. ዓመታዊ የስታትስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕቅዶች ለማዘጋጀት ትክክለኛና አስተማማኝ የስታትስቲክስ መረጃዎች መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና ስርዓት ባለው መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለዚህ ዓላማ ተፈጻሚነት የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከ1959 ጀምሮ ባለማቋረጥ የሀገሪቱን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሕዝብ ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች በስታትስቲክስ መጽሔት በማዘጋጀት ለመረጃ ተጠቃሚዎች ያሰራጫል።

በመሆኑም ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት ተጠናቆ በአራተኛው ሩብ ዓመት ላይ ለተጠቃሚዎች በመሰራጨት ላይ ነው። በመጽሔቱ ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች ይዘትም የሚከተሉትን ያካተተ ነው።

- የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድን ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት ውጤት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ (ፐብሊክ ፋይናንስ) መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የመድን (ኢንሹራንስ) መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ ሀገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

# 8. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

## 8.1 የሰው ኃይል ሁኔታ

በ1990 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የነበረው የሰው ኃይል ብዛት 2,666 ሲሆን ከእነዚህ መሃል 391ዱ ቋሚ 2,275 ደግሞ የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በ1990 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበሩ ቋሚ ሠራተኞች በሙያና በጾታ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

**በ1990 በጀት ዓመት የነበሩ ቋሚ ሠራተኞች በሥራ መደብ እና በጾታ**

| የሥራ መደብ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ባለሙያዎች | 114 | 13 | 127 |
| መለስተኛ ባለሙያዎች | 116 | 23 | 139 |
| የአስተዳደር፣ የሂሣብ፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት | 58 | 67 | 125 |
| ድምር | 288 | 103 | 391 |

## 8.2 የሰው ኃይል ሥልጠና

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች በስታትስቲክስ መረጃ አሰባሰብ፣ በመረጃ ቅንብር፣ በመረጃ ትንተና፣ በፕሮጀክትና በሪፖርት ዝግጅት እንደዚሁም በሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ያላቸውን ዕውቀት ከፍ በማድረግ የሥራ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ከሐምሌ 1 ቀን 1989 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1990 ድረስ የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተለው ተከናውኗል።

ሀ. ለግብርና ናሙና ጥናት፣ ለሰብል ትንበያ ጥናት እና ለዋጋ ጥናቶች በዋናው መሥሪያ ቤት ለመሥሪያ ቤቱ ባለሙያዎች እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ከነሐሴ 5 ቀን 1989 ጀምሮ ለ6 ቀናት የአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ አሠልጣኞች ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመሄድ ለተቆጣጣሪዎችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች ከነሐሴ 15 ቀን 1989 ጀምሮ ለ10 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

ለ. በሶማሌ ብሔራዊ ክልል ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ላይ ለተሳተፉ ተቆጣጣሪዎችና መረጃ ሰብሳቢዎች በየደረጃው ሥልጠና ተሰጥቶ ተግባሩን አከናውነዋል።

ሐ. በዚህ በጀት ዓመት በመካሄድ ላይ ለነበረው አገር አቀፍ የማዳበሪያ አጠቃቀም መሠረታዊ መረጃዎች ቅኝት እና በሐረሪ ብሔራዊ ክልል በመካሄድ ላይ ላለው አጠቃላይ የግብርና እንቅስቃሴ ጥናቶች ላይ ለተሳተፉ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ ተቆጣጣሪዎችና ሌሎች ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።

መ. በመረጃ ቅንብር ለሚሳተፉ ኢዲተርሽ ኢንኮደርስ (Data Entry Operators)ና ቬሪፋየርስ ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሠ. በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት እንደዚሁም በጤናና በአመጋገብ ጥናቶች ለተሳተፉ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤት የአሰልጣኞች ሥልጠና ከየካቲት 9-15 የተካሄደ ሲሆን ለመረጃ ሰብሳቢዎች ደግሞ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከየካቲት 24-መጋቢት 3 ሰልጠና ተሰጥቷል።

ረ በመስሪያ ቤታችን የፋይናንስ ስታቲስቲክስ ሥራን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች EROTRACE SOFTWARE አጠቃቀም ላይ ከ COMESA በተገኘ ድጋፍ ከውጭ በመጣ ባለሙያ የ10 ቀናት ስልጠና ከመሰጠቱ በተጨማሪ ሁለት ባለሙያዎችም በዚሁ መስክ በዛምቢያ/ ሉሳካ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

ሰ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ሦስት ሠራተኞች በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ይኸውም ሁለቱ በስታቲስቲክስ ፣ አንዱ በስነ-ሕዝብ ትምህርት ፤ በውጭ ሀገር በሚሰጥ ሥልጠና ደግሞ ሰባት ሠራተኞች ማለትም በዩጋንዳ ማከራሬ ዩኒቨርስቲ አምስቱ በስታቲስቲክስ፣ ሌላ አንድ ደግሞ በመረጃ ማቀነባበር ትምህርት እንደዚሁም በጋና ዩኒቨርስቲ አንድ ሠራተኛ በስነ-ሕዝብ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ተልከዋል።

## 9. የበጀት አጠቃቀም

ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ለ1990 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 49,746,022.66 የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 4,112,600፣ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 45,633,422.66 የተፈቀደ ነው። ይኸም ከተፈቀደው ጠቅላላ በጀት ውስጥ 8.27% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን 91.73% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው። እንደዚሁም ለካፒታል በጀት ከተፈቀደው 66.71% ለተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ሲሆን ቀሪው 33.29% ደግሞ ለሶማሌ ብሔራዊ ክልል ድጋሚ ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ማስፈጸሚያ የተመደበ ነው።

## 10. ማጠቃለያ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በሥራ ሂደት ያጋጠሙትን ችግሮች በመንግሥት፣ በእርዳታ ሰጪና አለም አቀፍ ድርጅቶች እገዛ እንደዚሁም በሠራተኞቹ ጥረት የተሰጠውን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ተወጥቷል፡፡ እንደዚሁም በሐገራችን ያለውን የስታትስቲክስ አጠቃቀምን ለማጎልበትና በዚህ መስክ የሚወጣውን የሐገር ሐብት በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዲቻል የሚከተሉት ጉዳዮች ግንዛቤ ሊያገኙ ይገባል፡፡

መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የስታቲስቲክስ ጥናቶች ስኬታማነት የመረጃ ምንጮች የሆኑት ግለሰቦች፣ የተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋሞች በአጠቃላይም ሕብረተሰቡ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ለየጥናቱ ውጤቶች ወቅታዊነትና አስተማማኝነት መረጋገጥ የየጥናቱ መረጃ ምንጮች የጥናቶቹን አላማዎች በሚገባ በመረዳት ተፈላጊውን መረጃ መስጠት መብትና ግዴታ አድርገው ማየት ይኖርባቸዋል፡፡ ከቤተሰቦችም ሆነ ከድርጅቶች የሚሰበሰቡ የስታቲስቲክስ መረጃዎች በፍፁም ምስጢራዊነት ተጠብቀው ሠፋ ባለ የአስተዳደርና የጂኦግራፊ ክልል ማለትም በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በገጠር...ወዘተ ደረጃ ማጠቃለያ ጭብጦችንና አመልካቾችን ለማስገኘት የሚያገለግሉ እንጂ በተናጠል በቤተሰብ ወይም በድርጅት ደረጃ የሚገኘው መረጃ በራሱ ጥቅም ላይ እንደ.ውል የማይደረግ መሆኑን በመረዳት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የስታቲስቲክስ ጥናቶች መሳካት ከሕብረተሰቡ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር እንዲደረግለት ይገባል፡፡

የስታቲስቲክስ ጥቅምና አስፈላጊነት በሁሉም የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚገለጽ በመሆኑ በርካታ ድርጅቶችና መ/ቤቶች ከኃላፊነታቸውና ከሥራ ድርሻቸው ጋር በሚጣጣም መልኩ ከውስን እስከ መጠነ-ሠፊ (ለምሳሌ በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ ወዘተ ደረጃ) የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ይጠቀማሉ፣ መጠቀምም ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት በሚደረገው ጥረት የሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከሀገሪቱ የስታቲስቲክስ መረጃ ዋነኛ ማዕከል ከሆነው ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ጋር በቅንጅት የሚሰሩበትን መንገድ ማሰብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህንን ማድረግ ባንድ በኩል የሐገር ሀብት ብክነትን መቆጣጠር ሲቻል በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ዓይነት አላማና የሽፋን መጠን ያላቸውን ጥናቶች በሁለትና ከዚያ በላይ ድርጅቶች ያለቅንጅት ለየብቻ በማካሄድ ሊከሰት በሚችል የውጤት ልዩነት የመረጃውን ተጠቃሚዎች ግራ ማጋባትን ማስወገድ ይችላል፡፡